# የወላጆች እና የተማሪዎች መብቶች ዓመታዊ ማሳወቂያ

## የት/ቤት ትብብር ኮሚቴ

## የተማሪ ክፍያዎች፣ ቅጣቶች እና ዋጋዎች

## የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና የግላዊነት አዋጅ

## ርዕስ VI፣ IX፣ ADA፣ ክፍል 504

## የተማሪ ዘር ወይም ጎሳ መለየት

## የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርት

## የተማሪ ፀባይ እና ሥነ-ምግባር

## ማንም ልጅ ወደኋላ አይተውም

## የምርጫ ት/ቤት

## ትንኮሳ

## ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች



የዴንቨር ት/ቤቶች ይህን በሕጋዊ መስፈርቶች መሠረት ያቀርብላችኋል። ይጠቅማችኋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። በዚህ ውስጥ የተጠቀሱ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች መከለስ እና መሻሻል የሚችሉ ናቸው። የትምህርት ቦርዱ ፖሊሲዎች የተናጥል ቅጅዎች በእያንዳንዱ የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤት እና በDPS ድረ ገጽ ይገኛሉ፦ www.dpsk12.org – የት/ቤት ቦርድ - ፖሊሲዎች።እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ የት/ቤትዎን ርዕሰ መምህር ወይም በ720-423-3400 TTY-TDD 720-423-3741 ወደ እንኳን ደህና መጡ ማእከል ሥልክ ይደውሉ።

ጁን 2011

## የተማሪ ክፍያዎች፣ ቅጣቶች እና ዋጋዎች

የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች ("DPS" ወይም "ዲስትሪክቱ") በርዕሰ-መምሩ ጽ/ቤት የሚመረመረው የJQ ፖሊሲ ክፍያዎች እና ወጭዎችን እንደሚከተለው ይወስናል፡-

- በመደበኛ ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ወሳኝ ለሆኑ የመማሪያ መጽሐፍት ክፍያ የለም፤
- ከመሠረታዊ መስፈርቶች በላይ እና/ወይም በተማሪው ሊያዙ የሚገቡ የአቅርቦት ወጭዎችን ያስከፍላል*፣
- ለኢንተርስኮላስቲክ አትሌቲክስ*፣
- በየአመቱ አስፈላጊ ለሆነው ለኢንተርስኮላስቲክ አትሌቲክስ የአካላዊ ምርመራ እናስከፍላለን - የወላጅ/የአሳዳጊ ኃላፊነት፤
- ለቅድሚያ ምደባ መጽሐፍት እና ፈተናዎች ያስከፍላል፣
- ለጠፉ/ለተበላሹ መማሪያ እና የቤተመጽሐፍት ያስከፍላል፣ እንዲሁም
- ሌሎች – የDPS JQ. ፖሊሲን ይመልከቱ።

የራሳቸው ንብረት ለሚያደርጓቸው የቁሳቁሶች መሠረታዊ ወጭ ካልሆነ በስተቀር ድሃ ተማሪዎች ምንም ክፍያ፣ ቅጣት፣ ወይም ዋጋ አይከፍሉም። ድሃ ተማሪ የሚባለው በብሄራዊ የገቢ ድህነት መመሪያ መሠረት የነፃ ወይም የቅናሽ-ዋጋ ምሳ የሚያገኝ ተማሪ ነው። ወላጅ ወይም አሳዳጊ ልጁ ለዚህ ብቁ ይሆናል ብሎ የሚያምን ከሆነ የርዕሰ መምህር ጽ/ቤትን ሊያነጋግር ይችላል።
*እነዚህ ክፍያዎች የሚተገበሩት ተማሪው በእንቅስቃሴዎቹ ለመሳተፍ ከመረጠ ብቻ ይሆናል።*

## የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና የግላዊነት አዋጅ ("FERPA")

DPS በFERPA መሠረት ስላሉት መብቶቻቸው ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ይህንን አመታዊ ማስታወቂያ ይሰጣል። የተማሪ ማኅደሮችን/ተማሪን የሚመለከት መረጃን ማውጣት (የJRA/JRC ፖሊሲ) በዴንቨር የሕዝብ ት/ቤት እና በDPS ድረ ገጽ ይገኛል። www.dpsk12.org – የት/ቤት ቦርድ - ፖሊሲዎች። በወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም በብቁ ተማሪዎች የመብት ጥሰትን የሚመለከት ቅሬታ ካለ ለDenver Public Schools, Office of Student Records, 900 Lincoln St., Denver, CO 80203 ወይም ለFamily Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Ave መላክ ይችላሉ።

***<u>መብቶች:-</u>***የፌዴራል እና የክልል/ስቴት ሕጎች የተማሪ የትምህርት ማህደሮች ግላዊነትን/ሚስጢራዊነትን ያስጠብቃሉ። ሕጉ ለወላጆች እና ብቁ (ከ18 ዓመት እና ከዚያ በላይ) ለሆኑ ተማሪዎች የማየት ጥያቄው ለዲስትሪክቱ ከቀረበ ከ45 ቀናት በኋላ ማኅደራቸውን የማየት እና የመገምገም፣ ተሳስተው ወይም ተዛብተው የተገኙ መረጃዎችን ት/ቤቱ እንዲያስተካክል የመጠየቅ፣ እንዲሁም በሕግ በተቀመጠው እና በዲስትሪክቱ የJRA/JRC ፖሊሲ መሠረት ያለ ወላጅ/ብቁ ተማሪ የጽሑፍ ስምምነት መረጃ እንዳይወጣ የመቆጣጠር መብት ይሰጣቸዋል። የተማሪዎች ማኅደሮች ቅጅዎች ለወላጆች/ብቁ ተማሪዎች ሲጠይቁ የሚሰጣቸው ሲሆን ክፍያውም በገጽ ከ$1.25 አይበልጥም።

***<u>ማኅደሮችን የመገምገም/የመመርመር ድንቦች:-</u>*** ተማሪው ከተመረቀ ወይም ካቋረጠ ወላጆች ወይም ብቁ ተማሪዎች ሊመረምሩት የሚፈልጉትን ማህደር(ሮች) ለይቶ ለማሳወቅ ለት/ቤቱ ርዕሰ-መምህር ወይም ለዲስትሪክቱ የተማሪ ማህደር ጽ/ቤት በጽሑፍ ማስገባት አለባቸው። የርዕሰ-መምህር ወይም የዲስትሪክቱ ጽ/ቤት ሠራተኞች የሚያዩበትን ሁኔታ ያመቻቹ እና ለወላጅ ወይም ለብቁ ተማሪ ማህደሮቹ ሊታዩበት ስለሚችሉ ቦታ እና ሰዓት ያሳውቃሉ። በክረምት (ሳመር) አብዛኛውን ጊዜ የተናጥል ት/ቤት ጽ/ቤቶች ዝግ ሊሆኑ ይችላሉ። በት/ቤት ውስጥ ያሉትን የት/ቤት ማህደሮች የሚፈልጉ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የትምህርቱ አመት ከማለቁ በፊት ቅጂዎቹን እንዲጠይቁ እናሳስባለን።

***<u>ማኅደሮችን የማሻሻያ ደንቦች:-</u>***ማህደሩ እንዲስተካከል የሚፈልጉ ወላጆች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች፣ መስተካከል ያለበትን የማህደሮች ክፍል በግልጽ ለይተው በማስቀመጥ፣ እና ማስተካከያው የተጠየቀበትን ምክንያት በመግለጽ ለት/ቤቱ ርዕሰ መምህር መፃፍ አለባቸው። ዲስትሪክቱ በወላጆች ወይም ብቁ በሆኑ ተማሪዎች የተጠየቀውን ላለማስተካከል ከወሰነ ለወላጆች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ውሳኔውን አሳውቆ ስለጥያቄአቸው እንዲጣራላቸው ይግባኝ የማለት መብት እንዳላቸውም ይመክራቸዋል። ስለጥያቄአቸው እንዲጣራላቸው ይግባኝ የማለት መብት እንዳላቸው ሲገለጽላቸው ስለማጣራት ሂደቶች/ደንቦችም ተጨማሪ መረጃ ይሰጣቸዋል።

***<u>ያለቅድሚያ ስምምነት መረጃን ስለማውጣት:-</u>***ያለ ቅድሚያ ስምምነት መረጃን ለሌላ ማካፈል የሚፈቀድበት አንድ ሁኔታ ህጋዊ የትምህርታዊ ፍላጎቶች ላላቸው የት/ቤት ባለስልጣናት ነው። የት/ቤት ባለስልጣን ማለት በዲስትሪክቱ የተቀጠረአስተዳድር፣ ሱፐርቫዘር፣ ኢንስትራክተር፣ ወይም (የጤና እና የህክምና እንዲሁም የሕግ አስከባሪ ክፍል ሠራተኞችን ጨምሮ) የድጋፍ ሰጭ ባልደረቦች፣ በት/ቤት ቦርድ ውስጥ የሚያገለግል ሰው፣ የተፈቀደለት በጎ ፈቃደኛ፣ እንደ የሥነ-ምግባር ወይም ቅሬታ ኮሚቴ ባለ በአንድ ሕጋዊ ኮሚቴ ውስጥ የሚያገለግል ወይም ሌላ የሕጋዊ ኮሚቴ አባል ሥራውን እንዲሰራ የሚያግዝ ወላጅ ወይም ተማሪ ማለት ነው። የት/ቤት ባለስልጣን ደግሞ ዲስትሪክቱ የራሱን ሠራተኞች በመጠቀም ፋንታ አገልግሎት እንዲሰጡት ኮንትራት የሚሰጣቸው ነገር ግን በዲስትሪክቱ ቁጥጥር ሥር ያሉ እና በግል ደረጃ ሊታወቅ ይሚችል መረጃን ላለማሰራጨት የተስማሙ (እንደ ጠበቃ፣ ኦዲተር፣ የሕክምና አማካሪ ወይም ወጌሻ/ቴራፒስት ያሉ) ግለሰቦች ወይምድርጅቶች ማለት ነው።

ዲስትሪክቱ የት/ቤት ባለስልጣናት ለሕጋዊ የትምህርታዊ ሥራ ተፈላጊ የሆኑ የትምህርታዊ ማህደሮችን ብቻ ማየታቸውን/መመርመራቸውን ለማረጋገጥ ተቀባይነት ያላቸውን ዘዴዎች ይጠቀማል። የት/ቤት ኃላፊዎች ሕጋዊ የትምህርታዊ ፍላጎት የሚኖራቸው ለሚከተሉት አላማዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የትምህርት ማህደርሲመመርመሩ ነው፡-ሀ) በተማሪው ትምህርታዊ ልማት ውስጥ ለወላጅ ወይም ለብቁ ተማሪ እገዛ ለማድረግ ከተማሪ ማኅደር መረጃ ለማግኘት፣ ለ) ማህደሩን ለማስተካከል እገዛ ለማደረግ፣ ሐ) በአስተዳደር ሠራተኛ የፀደቀ ትምህርታዊ ምርምር ለማድረግ፣ ወይም መ) ጤናማ እና የተስተካከለ አካባቢን ለማስጠበቅ።

ጥያቄ ሲቀርብለት፣ ዲስትሪክቱ ተማሪው እንዲመዘገብ ለሚፈልግበት፣ ወይም ቀደም ብሎ የተመዘገበበት ለሌላ የት/ቤት ዲስትሪክት መረጃው የሚሰጠው የተማሪውን ምዝገባ ወይም መዛወር አስመልክቶ እስከሆነ እና በስቴት ሕግና በዲስትሪክቱ ፖሊሲ መሰረት እስከሆነ ድረስ ያለምንም ፈቃድ አሳልፎ መስጠት ይችላል። ከቀድሞ ዲስትሪክት ያለውን የዲስፐሊን መረጃ ጨምሮ ከተማሪው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ላለው ለእያንዳንዱ መምህር እና አማካሪ ሙሉ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን፣ መረጃውን የሚቀበለው ግለሰብ የመረጃውን ምስጢራዊነት መጠበቅ ይኖርበታል፣ በምንም መልኩ መረጃውን ለሌሎች አሳልፎ መስጠት አይችልም።

***<u>የማውጫ መረጃ፦</u>***ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቃት ያለው ተማሪ ከምዝገባው ጊዜ ጀምሮ በሁለት ሳምንት ውስጥ ለበላይ ተቆጣጣሪ በጽሁፍ ተቃውሞ ካላቀረበ በስተቀር DPS "የማውጫ" መረጃ ይፋ ሊያደርግ ይችላል። ማውጫ መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል፦ ስም፣ የትውልድ ቀን፣ ጾታ፣ በኦፊሴል ተማሪው ተሳትፎ የሚያደርግባቸው እንቅስቃሴዎች፣ የአትሌቶች ክብደት እና ቁመት፣ የተቀባላቸው ዲግሪዎች እና ሽልማቶች፣ ከትምህርት ቤት የቀረባቸው ቀናት እና ፎቶግራፎች።

*የህክምና መረጃ፦*-የመረጃው መታወቅ የተማሪውን ወይም የሌሎች ግለሰቦችን ጤንነት ወይም ደህንነት ለማስጠበቅ አስፈላጊ ከሆነ በትምህርት ማህደር ላይ የሚገኝን፣ በግል የሚታወቀውን መረጃ DPS ከድንገተኛ ሁኔታ ጋር ግኑኝነት ላላቸው ተገቢ ወገኖች ይፋ ሊያደርግ ይችላል።

### የተማሪ መብቶች ማሻሻያ ጥበቃ ("PPRA")

PPRA የዳሰሳዊ ጥናቶችን፣ ለገቢያ ጥናት ሲባል መረጃን መሰብሰብ እና መጠቀምን እና እንዲሁም የተወሰኑ የጤና ምርመራዎችን በተመለከተ ለወላጆች የተወሰኑ መብቶችን ይሰጣል። እነዚህም የሚከተሉትን መብቶች ያካትታሉ፥

- ዳሰሳዊ ጥናቱ የሚደረገው በከፊል ሆነ በሙሉ በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት "(ED") ወጪው የሚሸፈን ከሆነ፣ ከሚከተሉት ጥበቃ የሚደረግላቸው ነገሮች ("ጥበቃ የሚደረግለት መረጃ ዳሰሳዊ ጥናት")፣ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን የያዘ መረጃ የሚፈልግ ዳሰሳዊ ጥናት ሲኖር ተማሪዎች መልስ ከመስጠታቸው በፊት **ስምምነት** ማግኘት ያስፈልጋል።
    1. የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጆች ፖለቲካዊ ወገንተኝነት ወይም እምነት፣
    2. የተማሪው ወይም የተማሪው ቤተሰብ ሥነ-አዕምሯዊ ወይም ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች፣
    3. የወሲብ ባሕርይ ወይም አመለካከቶች፣
    4. ሕገወጥ፣ ፀረ-ማኅበረሰብ፣ ራስን የመወንጀል ወይም የማዋረድ ባሕርይ፣
    5. ከመላሾች ጋር ቅርብ የቤተሰብ ትስስር ያላቸውን ሌሎች ሰዎችን መውቀስ፣
    6. በሕጋዊ መልኩ ታውቆ ዕውቅና የተሰጠው ዝምድና፥ ለምሳሌ ጠበቃ፣ ዶክተር ወይም የሃይማኖት አባት፣
    7. የተማሪው ወይም የወላጆቹ ሃይማኖታዊ ልማዶች፣ ወገንተኝነቶች ወይምእምነት፣ ወይም
    8. በሕጉ መሰረት የፕሮግራም ተገቢነትን ለመወሰን ከሚጠየቀው ውጪ የሆነ ገቢ።

- ***ማስታወቂያ መቀበል እና ተማሪን ከሚከተሉት ዕድሎች ማስወጣት፥***
    1. የገንዘብ ምንጩ ሳያገናዝብ ማናቸውም ሌላ ጥበቃ በሚደረግለት መረጃ ላይ የሚደረግ ዳሰሳዊ ጥናት፣
    2. ማንኛውም በት/ቤቱ ወይም በወከለው የሚተዳደር ድንገተኛ-ያልሆነ ተዛማች የአካላዊ ምርመራ ወይም ማጣራት እንደ ቅድመ-ሁኔታ የሚያስፈልግ፣ ነገር ግን የተማሪውን አጣዳፊ የጤና እና ደህንነት ለማስጠበቅ የማያስፈልግ ከመስማት እና ከማየት ወይም ከስኮሊኦሲስ /scoliosis/ ማጣሪያ በስተቀር፣ ወይም በመንግስት /ስቴት/ ሕግ መሠረት ከሚፈቀድ ወይም ከሚፈለግ ማንኛውም የአካላዊ ምርመራ ወይም ማጣሪያ በስተቀር፣ እና
    3. ከተማሪዎች የተገኘ መረጃን በመሰብሰብ፣ ለሌላ በመግለጽ ወይም ለንግድ ሥራ ዓላማ በመጠቀም ላይ ያተኮሩ እንቅስቃሴዎች ወይም ለሌሎች መሸጥ ወይም ማሰራጨት።
- **በመጠየቅ እና ከመጠቀም በፊት መመርመር፦**
    1. ጥበቃ የሚደረግላቸው የተማሪዎች መረጃ ዳሰሳዊ ጥናቶች፣
    2. ከላይ ለተጠቀሱት ለማናቸውም የንግድ ሥራ፣ ሽያጭ ወይም ሌላ የስርጭት ዓላማ መረጃን ከተማሪዎች ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋሉ መሳሪያዎች፣ እና
    3. እንደ ሥርዓተ-ትምህርቱ አንድ አካል ጥቅም ላይ የዋሉ መማሪያ ቁሳቁሶች።

እነዚህ መብቶች ከወላጅ ዕድሜው 18 ዓመት ወደ ሞላው ተማሪ ወይም በመንግስት/ስቴት ሕግ መሰረት ለተፈቀደለት/ነጻ ለወጣ ታዳጊ ይተላለፋሉ።

ዲስትሪክቱ ከወላጆች ጋር በመመካከር፣ ስለነዚህ መብቶች እንዲሁም ጥበቃ የሚደረግላቸው መረጃዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ የተማሪ ግላዊነትን ለማስጠበቅ እና ለንግድ ሥራ፣ ሽያጭ፣ ወይም ሌላ የስርጭት ዓላማ ስለሚደረግ የመረጃ ስብሰባ ፖሊሲዎችን አርቅቆ በማጽደቅ በሥራ ላይ ያውላል። ከዚህ በታች የተሰጠው ዓመታዊ ማሳወቂያ የሚያስፈልጋቸው እንቅስቃሴዎች እና ዳሰሳዊ ጥናቶች ዝርዝር ነው፥

- ✓ ለንግድ ሥራ፣ ለሽያጭ ወይም ለሌላ የማሰራጨት ዓላማ የግል መረጃን መሰብሰብ፣ ማውጣት ወይም መጠቀም፣
- ✓ በከፊልም ሆነ በሙሉ በED የገንዘብ ድጋፍ ለማይደረግለት ማናቸውም ጥበቃ የሚደረግለት መረጃ ዳሰሳዊ ጥናት አያያዝ፣ እና
- ✓ ከላይ እንደተገለጸው ማንኛውም ድንገተኛ-ያልሆነ ተዛማች የአካላዊ ምርመራ ወይም ማጣራት።

እንደ ዩ.ኤስ የፖስታ አገልግሎት ወይም ኢሜይል ያሉትን መንገዶች በመጠቀም ዲስትሪክቱ ወላጆችን በተወሰኑ እንቅስቃሴዎች ወይም ከላይ በተገለጹት ዳሰሳዊ ጥናቶች ላይ ተማሪዎች ከመሳተፋቸው በፊት እንዲያውቁት ያደርጋል እንዲሁም በተጠቀሰው እንቅስቃሴ ወይም ዳሰሳዊ ጥናት ላይ ልጃቸው እንዳይሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ ይህንኑ ምርጫ ለወላጆች ያቀርብላቸዋል። በእያንዳንዱ አዲስ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ እያንዳንዱ ት/ቤት ከላይ የተዘረዘሩት ዳሰሳዊ ጥናቶች/እንቅስቃሴዎች መቼ እንደሚከናወኑ ግምታዊ የጊዜ ሰሌዳ ለወላጆች ይሰጣል።

የትምህርት ዓመቱ ከጀመረ በኋላ እንዲደረጉ ለተያዙ ዳሰሳዊ ጥናቶች እና እንቅስቃሴዎች። ወላጆች ስለታቀደው እንቅስቃሴ እና ከላይ ስለተዘረዘሩት ዳሰሳዊ ጥናቶች በቂ የሆነ ማሳወቂያ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፣ እናም በተጠቀሰው እንቅስቃሴ ወይም ዳሰሳዊ ጥናት ውስጥ ልጃቸው እንዳይሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ ይህንኑ ምርጫ ይቀርብላቸዋል። ወላጆች በተጨማሪ ማናቸውም አግባብነት ያላቸውን ዳሰሳዊ ጥናቶች በቅድሚያ እንዲያዩአቸው/እንዲገመግሟቸው ዕድሉ ይሰጣቸዋል።

### ለወታደራዊ መልማዮች መረጃ አሳልፎ መስጠት

ወላጅ/ብቁ ተማሪ በየዓመቱ ለዋናው ተቆጣጣሪ (ሱፐርኢንቴንዳንት) መረጃው እንዳይሰጥ በጽሑፍ ካልተቃወሙ በስተቀር፣ መልማዩ አካል ጥያቄ በሚቀርብለት ጊዜ፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን ስም፣ የመኖሪያ አድራሻዎች እና የስልክ ቁጥሮች ለወታደራዊ መልማዮች መረጃ ይሰጣል። መልማዮቹ ይህን መረጃ ስለ ወታደራዊ አገልግሎቶች መረጃ ለመስጠት ብቻ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በቦርድ JRA/JRC ፖሊሲ መሰረት፣ ዲስትሪክቱ ይህ መረጃ እንደሚለቀቅ ለወላጆች በቅድሚያ የጽሑፍ ማሳወቂያ ይሰጣል። ከዚህ ማሳወቂያ ጋር መረጃው እንዳይሰጥ ለመቃወም የሚቻልበት መንገድ ዝርዝር መረጃ አብሮ ይላካል። ወላጁ ወይም ተማሪው የተማሪው ስም፣ አድራሻ እና የስልክ ቁጥር ዝርዝር ከወላጅ በሚሰጥ የጽሑፍ ፈቃድ በቅድሚያ ሳይገኝ መረጃው እንዳይሰጥ መጠየቅ ይችላሉ።

## ለሜዲከኤድ /Medicaid/ መረጃ አሳልፎ መስጠት

እንደ ሜዲከኤድ አገልግሎት ሰጪ፣ DPS በ DPS ለተመዘገቡ ተማሪዎች የሜዲከኤድ ተገቢነት መረጃዎችን ከጤና እንክብካቤ ፖሊሲ እና ፋይናንሲንግ (HCPF) ሊያገኝ ይችላል። HCPF በግዛቱ/በስቴቱ ውስጥ ስልጣን የተሰጠው የሜዲከኤድ ወኪል ድርጅት ነው። በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ለሜዲከኤድ ያላቸውን ብቁነት ለማረጋገጥ ሲባል የስም፣ የትውልድ ቀን፣ እና የጾታ የማውጫ መረጃዎች ለHCFP ሊሰጡ ይችላሉ። ፕሮግራሙ በተገቢው መንገድ መከናወን እንዲችል ለሜዲከኤድ ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ያገኙትን የጤና እና የጤና-ነክ አገልግሎቶች ለሜዲከኤድ እና/ወይም ለዲስትሪክቱ ክፍያ ሰብሳቢ ድርጅት ሊላክ ይችላል። ለሁሉም ክንውኖች /transactions/ የተመዘገበው ቀን ሪኮርድ በDPS ት/ቤት ሜዲከኤድ /Medicaid / ጽ/ቤት ውስጥ ይቀመጣል።

## ርዕስ VI፣ IX፣ ADA፣ ክፍል 504

DPS ለምዝገባ ወይም ለትምህርት ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴዎች በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በእምነት፣ በትውልድ፣ በብሔራዊ ወይም የዘር ሐረግ፣ በጾታ፣ በዕድሜ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ልዩነት/መድሎ አያደርግም። ለአድልዎ ጉዳይ የቅሬታ ድንብ አለ። የመድልዎ ድርጊቶችን በተመለከተ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለU.S. Department of Education Office for Civil Rights, 1244 Speer Blvd., Denver, CO 80204-3582፣ ወይም በDPS ለአንድ ለዚህ ጉዳይ ለተመደበ/ለሚመለከተው ሠራተኛ በሚከተሉት አድራሻዎች ማቅረብ ይቻላል፡- ለተማሪዎች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር (900 Grant Street, Denver, CO 80203፣ ሁለተኛ ፎቅ፣ ሥ.ቁ. 720-423-3437 ወይም TTY-TDD- 720-423-3741) ለSection 504 of the Rehabilitation Act of 1973, (29 U.S.C. §794) እና ለAmericans with Disabilities Act, (42 U.S.C. §12101 et seq.) ጉዳዮች፤ Director Athletics (ሥ.ቁ.720-423-6173) ወይም ለሰው ሃብት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር (900 Grant Street, Denver, CO 80203፣ አምስተኛ ፎቅ፣ ሥ.ቁ. 720-423-3973) ለTitle IX of the Education Amendments of 1972 (20 U.S.C. §1681) የፆታ መድሎ ጉዳዮች።

በDPS ወይም በትምህርት እንቅስቃሴዎች ለመካፈል ለሚፈልጉ የአካለ ጉዳተኞች ጥያቄ ሲቀርብ ተገቢ መስተንግዶ ይደረግላቸዋል። እባክዎን ከእንቅስቃሴው ቢያንስ ከሶስት የስራ ቀናት ቀደም ብለው ት/ቤቱን ወይም መምሪያውን ያሳውቁ።

## የተማሪ ዘር ወይም ጎሳ መለየት

በፌደራል እና በስቴት ሪፖርት አደራረግ መስፈርቶችን ለማሟላት፣ DPS እያንዳንዱን ተማሪ በወላጅ/አሳዳጊ በተሰጠው መረጃ መሰረት በዘር ወይም በጎሳ ለይቶ አስቀምጧል። የትምህርት ቦርዱ በሜይ 1975 ባፀደቀው ውሳኔ መሰረት፣ ይህ ለይቶ ማወቅ እንደተደረገ ወላጆች በየዓመቱ እንዲያውቁት እንዲደረግ ያስገድዳል። ለልጅዎ የተመዘገበው ማንነት መለያ መረጃ ምን እንደሆነ ለማወቅ ከፈለጉ፣ ይህን መረጃ በልጅዎ ትምህርት ቤት በአካል በመገኘት መጠየቅና ማግኘት ይችላሉ። የተመዘገበው ማንነት መለያ ትክክል ሳይሆን ቢቀር፣ የት/ቤቱ ሠራተኛ ለእርማት አስፈላጊውን አካሄድ ስርዓት ያስረዳዎታል።

## የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርት

የአካል ጉዳት ያለበት ማናቸውም ብቁ በዴንቨር ነዋሪ የሆነ ተማሪ፣ ከ3 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ እስከ 21ኛ የልደት በዓሉ ድረስ የአካል ጉዳት የሌለባቸው ተማሪዎች ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎች ላይ ከሚጣሉ የግዴታ የአገልግሎት ክፍያዎች በስተቀር ምንም ክፍያ ሳይፈጽሙ ነጻ፣ ተገቢነት ያለው ሕዝባዊ ትምህርት የማግኘት መብት አለው። DPS ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር በጋራ በመሆን ዕድሜያቸው ከ3 ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናት በማኅበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊውን ግብዓት እና አገልግሎት እንዲያገኙ ልጆቹን ለይቶ ለማወቅ፣ ለመገምገም፣ ከትምህርት ቤት በፊት ለሚሰጥ ልዩ የእርዳታ አገልግሎት ለማግኘት ብቁ መሆናቸውን ለመወሰን እና ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ ይጥራል።

ማናቸውም ጥያቄዎች ተማሪው ለሚማርበት ት/ቤት ርዕሰ መምህር ወይም ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽ/ቤት (720-423-3437) መቅረብ አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ማግኘት ይችል ዘንድ እንዲገመገም ለመጠየቅ መብት አላቸው።

## የተማሪ ዲስፕሊን — JK ፖሊሲ (ደግሞም የተማሪ ጠባይ እና የዲስፕሊን እርምጃዎች — JK-R ፖሊሲን እና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ዲስፕሊን JKF ፖሊስን ይመልከቱ)

ጤናማ እና የተመቻቼ የሆነ እንዲሁም ካላስፈላጊ ረብሻ የፀዳ የት/ቤት ከባቢ የዲስትሪክቱን ተልዕኮ ለማሳካት ወሳኝ ነው፣ ይህም የተማሪዎች፣ የሥራ ባልደረቦች፣ የወላጆች፣ እና የማኅበረሰብ ጥምር ኃላፊነት ነው።

የተማሪ ፀባይ ደንቦችን፣ ለመማር ማስተማር አግባብነት ያላቸውን ባሕርያት፣ እና ተማሪዎችን በተግባራቸው ተጠያቂ ስለማድረግ በማሳወቅ DPS እያንዳንዱ ተማሪ ራስን-መግዛትን ለማሳካት ይጥራል። ቅድመ-መከላከል ትኩረት ይሰጠዋል፣ ችግሮችም ወዲያውኑ እንዲፈቱ ይደረጋሉ። አዎንታዊ የሆነ የት/ቤት ድባብ ለውጤታማ የድስፐሊን ፕሮግራም አስፈላጊ አካል ነው።

የሚከተሉት ድርጊቶች በግልፅ የተከለከሉ ናቸው፣ እናም በተማሪው ላይ የድስፐሊን እርምጃ የሚያስወስዱባቸው ይሆናሉ፡-

1. ታስቦበት ወይም በግድየለሽ ሁኔታ ሌሎች ሰዎች ላይ አካላዊ ጉዳት የማድረስ ስጋት የሚፈጥር ባሕርይን ጨምሮ ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለት/ቤት ሠራተኞች ደህንነት ወሳኝ የሆነ በት/ቤት ንብረት ላይ ወይም ውጭ ባሕርይ፣

2. ት/ቤቱ ለሌሎች ተማሪዎች ትምህርታዊ አገልግሎቶች/ዕድሎችን ለማቅረብ የሚያደናቅፍ ባሕርይ፣

3. በት/ቤት ንብረት፣ በት/ቤት ተሸከርካሪዎች ወይም በት/ቤት ዝግጅት ላይ ብጥብጥ የሚያስነሳ፣

4. በፖሊሲው በተገለጸው መሠረት አደገኛ (የጦር) መሳሪያን ማምጣት፣ መሸከም፣ መጠቀም፣ ወይም ይዞ መገኘ፣

5. ከወሮ-በላ ጋር የሚያያዙ ድርጊቶች እና እንደ ቀለም፣ የእጅ ምልክቶች፣ የግድግዳ ጋር ጽሑፎች፣ ለየት ያለ ልብስ፣ ጌጣጌጥ፣ የማስታወሻ ደብተሮች፣ የንግድ ምልክቶች ያሉ ከወሮበላነት ጋር የሚገናኙ ፀባይዎች እና ከጊዜ ወደ ጊዜ በት/ቤት አስተዳደሮች እንዲታገዱ/እንዲከለከሉ የተወሰነባቸው ሌሎች ከወሮበላነት ጋር ግንኙነት ያላቸው መገለጫዎች።

6. የአልኮል፣ የእፆች ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረነገሮችን በት/ቤት ንብረት ወይም በት/ቤት ተሸከርካሪ ውስጥ መሸጥ፣ ማሰራጨት፣ ይዞ መገኘት፣ መጠቀም ወይም በእነዚህ ተጽዕኖ ውስጥ መውደቅ፣

7. ድብድብ፣

8. ጥቃት፣

9. ዝርፊያ፣

10. ሌብነት፣ የሌላ ሰው ንብረት ማንሳት፣ ወይም መስበር እና መግባት፣

11. ትምባሆ መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት፣

12. እያወቁ የት/ቤት ሰራተኛ ላይ ልጆች ላይ ጥፋት አድርሰዋል በማለት በሃሰት ክስ ማቅረብ፣

13. ትንኮሳ፣

14. ማሸማቀቅ/ማስፈራራት

15. የት/ቤት ንብረት ወይም የሌሎችን ንብረትን በፈቃድ/እያወቁ ውድመት ወይም ብልሽት ማድረስ፣

16. ፀያፍነት ወይም አስቀያሚነት፣

17. በአካል ጉዳተኝነት፣ ጎሳ፣ ፆታ፣ ዘር፣ ሓይማኖት ወይም የፀታ ምርጫ ወይም የፆታ ማንነት ብቻ ሳይወሰን በእነዚህ ላይ ተመስርቶ ክብረ-ነክ አስተያየቶችን መስጠት፣

18. የግለሰብ አቋም ወይም ንጽሕናን አለመጠበቅ ተቀባይነት የለውም፣

19. የት/ቤት ዲስትሪክት ወይም የት/ቤት የአለባበስ ደንቦችን መጣስ ወይም ለየት ያሉ ልብሶችን መልበስ እንደድስፐሊን ችግር ይቆጠራል፣

20. አውቆ አለመታዘዝ ወይም ግልጽ የሆነ እና ተከታታይ አግባብ ያለውን ስልጣን መተው/መናቅ፣

21. በማንኛውም የት/ቤት ሠራተኛ ግለሰብ ወይም ንብረቱ ላይ ወይም የበጎ ፈቃድ አዋቂ ሰው ላይ ያነጣጠረ ጥቃት፣ የተዛባ ምግባር ወይም ማንኛውም የወንጀል ድርጊት፣

22. በት/ቤት ግቢ ውስጥ የብጥብጥ ወንጀል ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ድርጊት በአዋቂ ከተፈጸመ፣ ሌሎች ተማሪዎች ወይም የት/ቤት ሠራተኞች ቢሳተፉም ባይሳተፉም፣

23. በሰዎች ወይም በንብረት ላይ ቀጥተኛ ወይም ስውር ዛቻ ወይም ሥጋት፣

24. ት/ቤቱ ለሌሎች ተማሪዎች ትምህርታዊ አገልግሎቶች/ዕድሎችን የማቅረብ ችሎታውን በተደጋጋሚ የሚያደናቅፍ፣

25. የአዘውትሮ ረባሽ ተማሪ ድንጋጌ፣ ማለትም በተማሪው በራሱ ተነሳሽነት እያወቀ ክፍል ውስጥ፣ በት/ቤት ውስጥ፣ በት/ቤት መጫወቻ ቦታዎች ውስጥ፣ በት/ቤት ተሸከርካሪዎች ውስጥ፣ ወይም በተጓዳኝ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ወይም ዝግጅቶች ላይ በሚፈጽማቸው ቁሳዊ ወይም ከባድ ጥፋት ያስከተሉ በኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶች ምክንያት በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ ለሦስት (3) ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ያህል ከት/ቤት የታገደ።

የድስፐሊን ደንቦች ተገቢ አሰራር ሊኖራቸው፣ በወጥነት እና በእኩልነት ሊተገበሩ፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ ት/ቤት እና ክፍል ውስጥ ለመማር-ማስተማሩ ምቹ የሆነ ድባብ ሊፈጥሩ ይችላሉ። የአንድ ተማሪ በርዕሰ መምህሩ መታገድ ወይም በዋና ተቆጣጣሪው (ሱፐር-ኢንቴንዳንቱ) መባረር ለወላጅ የሚገለጸው በፖሊ እና በሕግ መሠረት ይሆናል። ወላጆች በስቴት ሕግ እና ዲስትሪክቱ JK ፖሊሲ መሠረት በአንዳንድ እርምጃዎች ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አላቸው። የተማሪ ሥነምግባር እና ድስፐሊን JK ፖሊሲ ቅጅዎች በርዕሰ መምህሩ ጽ/ቤት ወይም በሚከተለው የDPS ደረ ገጽ ላይ ይገኛሉ። www.dpsk12.org – የት/ቤት ቦርድ - ፖሊሲዎች።

## ምንም ልጅ ወደ ኋላ አይተውም - ሊታወቅ የሚገባው የወላጆች መብት

ትምህርት ቤት በመማር ላይ ያለ የማናቸውም ልጅ ወላጆች የተማሪ ልጃቸው የክፍል መምህር(ራን) ሙያዊ ብቃትን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ። የሚጠየቀው መረጃ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፥

- መምህሩ ለክፍል ደረጃው እና ለሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት የስቴት ፈተና ወስዶ ፈቃድ የተሰጠው ስለመሆን አለመሆኑ፣
- መምህሩ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ወይም በጊዜያዊነት በስቴት የተቀመጠውን መስፈርት ሳያሟላ እያስተማረ ያለ ስለመሆን አለመሆኑ፣
- የመምህሩ የመጀመሪያ ዲግሪ ዋና ትምህርት እና ማናቸውም መምህሩ ያሉት የምሩቅ ማረጋገጫዎች ወይም ያሉት ዲግሪዎች፣ የተማራቸው ዋና የትምህርት ዓይነትን ጨምሮ፣ እና
- ልጁ በተባባሪ ባለሙያዎች አገልግሎት እየተሰጠው ከሆነ በእነርሱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫዎችን መጠየቅ ይችላሉ።

ይህን መረጃ መጠየቅ የሚፈልጉ ወላጆች ለልጃቸው ት/ቤት ሥልክ መደወል አለባቸው። መረጃው በፖስታ ቤት በኩል ይላክላቸዋል።

በርዕስ 1 ት/ቤቶች እና በዕቅድ አወጣጥ 1% ለወላጅ ተሳትፎ በተቀመጠው መጠን መሰረት ወላጆች በት/ቤቱ ሰፊ/የትምህርት ቤት ማሻሻያ ዕቅዶች ላይ በዕቅድ አወጣጥ፣ ግምገማ እና ማሻሻል ሥራዎች የመሳተፍ መብት አላቸው። በተጨማሪ ወላጆች የት/ቤቱ ሥርዓተ-ትምህርት ትንተናን እና የልጃቸው

ትምህርታዊ ዕድገት ከሚፈለገው የተቀመጠው የብቃት መመዘኛ መስፈርት ደረጃ መድረስ አለመድረሱ ለመለካት የሚገመገምባቸውን የማወቅ መብት አላቸው። ወላጆች ልጃቸው በሚማርበት ተማሪዎች ወላጆች ከሆኑ ማለትም እንደ ጠባይ ማረሚያ እርምጃ ወይም ማስተካከያ ርዕስ 1 ት/ቤት ውስጥ ልጆቻቸው የሚማሩ ወላጆች በትምህርት ቤት ደረጃ ለሚወሰደው እርምጃ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተሳትፎ የማድረግ መብት አላቸው። እንዴት ተሳትፎ ማድረግ እንደሚችሉ ለማወቅ እባክዎ የእርስዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

ወላጆች የልጃቸውን ትምህርት ቤት ነፍስወከፍ NCLB ሪፖርት ካርድ የማየት እና የማግኘት መብት አላቸው። የት/ቤት ሪፖርት ካርድን በhttp://schoolforms.dpsk12.org/schoollist ወይም የታተመ ቅጅ በሥ.ቁ. 720-423-3054 በመደወል ማግኘት ይችላሉ።

## የምርጫ ት/ቤት

የDPS "ምርጫ" ሂደት ተማሪዎች የመኖሪያ አካባቢያቸውን የሚያገለግል ት/ቤት ላልሆነ የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤት ለማመልከት ያስችላቸዋል። ይህ የአሰራር ሂደት ከዴንቨር ከተማ ውጪ ለሚኖሩ ተማሪዎች ማመልከቻ እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣቸዋል። ሦስት የማመልከቻ ማቅረቢያ ወቅቶች አሉ፦ የመጀመሪያ ዙር፣ የሁለተኛ ዙር እና በአስተዳደር የሚደረግ ዝውውር ወቅቶች ናቸው። የመጀመሪያው ዙር ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት፣ ከጃኗሪ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ይደረጋል። ሁለተኛው ዙር የሚጀምረው ልክ የመጀመሪያው ዙር ምዝገባ እንዳለቀ ትንሽ ቆይቶ ሲሆን እስከሚቀጥለው የትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ሁለት ሳምንታት ድረስ ይካሄዳል። የአስተዳደራዊ ዝውውር በትምህርት ዓመቱ ቀሪ ጊዜ በሞላ ይካሄዳል።

በመጀመሪያው ዙር ካለው ክፍት ቦታ በላይ ብዙ ተማሪዎች ካመለከቱ፣ ተማሪዎች በሚሰጣቸው ቁጥር መሰረት እና ባላቸው ቅድሚያ የማግኛ ኮድ መሰረት (ቀደም ብለው በትምህርት ቤቱ መማር በመጀመራቸው፣ ወደየሚኖሩበት ቦታ በመመለሳቸው፣ በትምህርት ቤቱ የሚማር ወንድም/ እህት ስላላቸው፣ የዴንቨር ነዋሪ አመልካች በመሆን (በከተማዋ/በስቴት ድንበሮች ውስጥ የሚኖሩ) ነዋሪ ያልሆኑ እህት/ወንድሞች እና አመልካቾች)። ቦታ ሲኖር፣ የመጀመሪያ ዙር ማመልከቻ ተቀባይነት ያገኛል።

በሁለተኛ ዙር ማመልከቻ ጊዜ፣ ማመልከቻዎች እንደ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል ይስተናገዳሉ፣ እንዲሁም የመጀመሪያ ዙር አመልካቾች ቦታ ካገኙ በኋላ በሚኖረው ክፍት ቦታ ላይ ይመደባሉ።

የአስተዳደራዊ ዝውውርን ለማጠናቀቅ፣ ማመልከቻው በዲስትሪክት አስተዳዳሪ ተቀባይነት ከማግኘቱ ወይም ውድቅ ከመደረጉ በፊት ማመልከቻ በላኪው እና ተቀባዩ ት/ቤቶች ርዕሰ መምህራን በሁለቱም መሞላት እና መፈረም አለበት። ማመልከቻው ዝውውር የተጠየቀበትን ምክንያት እንዲጠቀስ ይጠይቃል። አስተዳዳራዊ ዝውውር በቦታ ጥበት ወይም በፕሮግራም አለመኖር፣ በዲሲፕሊን ወይም በደህንነት ምክንያቶች፣ በትምህርታዊ ምክንያት ወይም ጥያቄው የቀረበው በሴሚስተሩ ውስጥ ዘግይቶ የቀረበ ከሆነ ብቻ ውድቅ ሊደረግ ይችላል።

በተጨማሪም፣ ማንም ተማሪ ወደኋላ አይተውም በሚለው የ2001 ሕግ መሰረት፣ በርዕስ 1 ትምህርት ቤቶች አጎራባች አካባቢ የሚኖሩ እና ዓመታዊ የዕድገት ዒላማዎችን የማያሟሉ የDPS ተማሪዎች በሌሎች የDPS ትምህርት ቤቶች በDPS ፖሊሲ (ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጓጓዣ በRTD አውቶብሶች ይቀርባል) መሰረት መጓጓዣ ተሟልቶላቸው በሌሎች የDPS ት/ቤቶች የመማር አማራጮች ይሰጣቸዋል። ተማሪዎች ይህ አማራጭ እንዳለ እና ለእነርሱ የሚሆናቸው ከሆነ እንዲመርጡ እንዲያውቁት ደብዳቤ የሚላክላቸው ሲሆን ማመልከቻዎች ከልማዳዊ የምርጫ /Traditional Choice/ ጋር ይስተናገዳሉ።

### *ፆታዊ ጥቃት — JBB ፖሊሲ/ በቆዳ ቀለም ወይም በዘር፣ በብሔር፣ በፆታዊ ምርጫ፣ በፆታ ማንነት፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሃይማኖት (ተማሪ) የተነሳ የሚደርስ ጥቃት — JBBA ፖሊሲ*

በት/ቤት ዲስትሪክቱ ውስጥ ያለ ማናቸውም ተማሪ ከፆታዊ ጥቃት ወይም እንደ ዘር ወይም ቀለም፣ ብሔር፣ የየዘር ሀረግ፣ ፆታዊ ምርጫ፣ የጾታ ማንነት፣ የአካል ጉዳት ወይም ሃይማኖት ባሉ መሠረቶች ከሚደርሱ ጥቃቶች የጸዳ የመማር ዕድል ሊያገኝ ይገባዋል። የትንኮሳ ቅሬታዎች አግባብ ባላቸው የቦርድ ፖሊሲዎች መሠረት ወዲያውኑ ይመረመራሉ።

### የት/ቤት ሕተመት ደንብ/ኮድ - JICEA ፖሊሲ

DPS ተማሪዎች የመናገር እና የህትመት ነፃነት የማራመድ መብት እንዳላቸው የሚያረጋገጥ የሕትመት ውጤቶች ነጻነት ደንብን አጽድቋል፣ እና በተማሪዎች ሕትመት ውጤቶች ላይ የሚካተት፣ በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር ተደረገም አልተደረገ፣ ማንኛውም የሕትመት ይዘት በJICEA ወረዳ ፖሊሲ ውስጥ ከተጠቀሱት የተወሰኑት የሕትመት ይዘቶች በስተቀር ምንም ቅድሚያ ዕገዳ አይደረግበትም። የJICEA ፖሊሲ እና ከ JICEA-R ጋር የተያያዙ የተማሪዎች ሕትመቶች (የትምህርት ቤት ደንብ) በሚከተለው የDPS ድረ ገፅ፦ www.dpsk12.org – የት/ቤት ቦርድ - ፖሊሲዎች።

### *የፆታ ጥቃት መረጃ*

ከኮሎራዶ የፆታ ጥቃት ፈፃሚዎችን የማስመዝገብ ሕግ አፈፃፀም ደንብ ጋር ስለተያያዘ መረጃ የማህበረሰቡ አባላት ስለሚከተሏቸው ደንቦች መረጃ በሚከተለው ድረ ገፅ ላይ ይገኛል፦ http://www.dcj.state.co.us/odvsom/Sex_Offender/SO_Pdfs/schoolresourceguideregistration.pdf
እንዲሁም በሚከተለው በCDE ድር ጣቢያ፦http:www.cde.state.co.us/cdeprevention/download/pdf/school_sex_offender_guide.pdf.

ከዚህ በተጨማሪም፣ በተማሪዎች አገልግሎት ክፍል ውስጥ ፎቶ ኮፒ የማድረጊያ $2.00 በመክፈል የመመሪያውን ቅጂዎች ማግኘት ይቻላል። በዚህ ቦታ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ የማህበረሰቡ ዓባላት በነፃ ሰነዱን ማየት እና ከላይ በተጠቀሱት የድር ጣቢያዎቸ ላይ ያለምንም ክፍያ ሰነዱን ማውረድ ይችላሉ።

### የወላጅ የመገኘት (አቴንዳንስ) ግዴታ

እያንዳንዱ ወላጅ በኮሎራዶ ሕግ መሰረት ልጆቹ በቂ ትምህርት እና ስልጠና እንደሚያገኙ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። በዚህም መሠረት፣ ዕድሜው ከሰባት ዓመት በላይ እና ከአስራ ሰባት ዓመት በታች የሆነ ልጅ ማንኛውም ወላጅ ልጁ በት/ቤት እየተማረ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

## የIHBEA - እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ /English as a Second Language/ ፖሊሲ

**ዋና ቋንቋቸው ከእንግሊዝኛ ውጭ ለሆነ ልጆች ትምህርታዊ ዕድሎችን የማቅረብ የኮሎራዶ ስቴት ዓላማ በማክበር ዲስትሪክቱ ከመዋዕለ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ እንደነዚህ ዓይነት (ከእንግሊዝኛ ውጭ የሆነ) ልጆች ሕጎች እና የኮሎራዶ የትምህርት ዲፓርትመንት**

**በሚጠይቁት መሠረት ተስማሚ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚሰጥ ይሆናል። አሁን የሚሰራበት ሕግ በ1993 ተረቀቀ**
***ፀደቀ፡-መመሪያው የፀደቀበት ቀን***

**ሕጋዊ ማጣቀሻ /LEGAL REFS/:- C.R.S. 22-24-101 እስከ 22-24-105 (የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ደንብ)**
**1 CCR 301-10፣ ሕጎች 2224-R-1 እስከ 2224-R-3**

***ለተማሪዎች እና ለወላጆች የዲስትሪክት ፖሊሲ መመሪያ***
በጣም በቅርብ ጊዜ የተሻሻለዎን የዲስትሪክቱን ፖሊሲዎች ቅጅ ለማግኘት እባክዎ የDPS ድር ጣቢያ፡- www.dpsk12.org/policies ይጎብኙ ወይም በት/ቤትዎ ቅጁን ለማየት ይጠይቁ።


**ዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች**
**900 Grant Street – Denver Colorado 80203**
**ሥ.ቁ. 720-423-3400 TTY-TDD 720-423-3741**